# የዝቋላ ተራራ ትዝታ…

ገ/ኢ.ጐርፉ

የዝቋላ ተራራ ከአዲስ አበባ ከተማ በስተደቡብ ሓምሳ ኪሎ ሜትር እንኳን በማይሞላ ርቀት የሚገኝ፣ ከስዕሉ እንደሚታየውም በአዲስ አበባ ከተማና በተራራው መካከል ያለው ፊት ለፊት ለጥ ያለ የአድኣ ወረዳ ሜዳ ነው።



ከዚህ ቀጥሎ የምተቸው በግምት ከዓርባ ዓመት በፊት ወጣት፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆኜ፣ በእግሬ ዝቋላ ለጉብኝት ተጉዤ፣ ያየሁትና የተመለከትኩት ነው።

ዛሬ ሁኔታው ብዙ መለወጡን አላውቅም፣ ተለውጦም ከሆነ በቅርብ ጊዜ ያዩት አንባቢዎች፣ አስተያየታቸውና ምን ያህልስ ለውጥ መኖሩ ቢጽፉ ደግ ነው።

ከተራራው ፊት ለፊት የሚታየው የአድኣ ሜዳ በክረምትና በበልግ ወራት በብዙ ልምላሜ፣ በታወቀው የአድኣ ማኛና ሰርገኛ ጤፍ፣ በብዙ ሌላም አዝርእት ይልብሳል። በበጋ ግን ደረቅና የውሃ ችግር በጣም የሚያጠቃው ቦታ ነው። ኗሪዎቹ በማለዳ ከሩቅ ተጉዘው፣ የተገኘውን የውሃ ጥርቃሚ ኩሬ፣ ጐርፍ ያመጣውን ወራጅ በትንሽ ጎድጓዳና ረባዳ ቦታ ተከማችቶ፣ በእሾኽ ኣጥር የተከተረውን ውሃ ቀድተው፣ በአህዮችና በሌላም ከብቶች ጭነው ወደየቤታቸው ውስደው ለየዕለቱ የሚያስፈልጋቸውን ይጠቀማሉ።

ኩሬውና የተከተረው ውሃ ግን ኣገልግሎቱ ለሰው ብቻ ሳይሆን ለከብትም፣ ለሰማይ አዕዋፍና ለሜዳ አውሬም በመሆኑ፣ ከብቶቹም ከዚያው ጠጥተው ከዚያው ስለሚጸዱ፣ ውሃው በጣም ቆሻሻና ለጤናም እጅግ ኣደገኛ ነው። ግን ሌላ ከየት ይምጣ! ስለዚህም ውሀ የጠማን መንገደኞች ስንለምናቸው፤ "ቢሻን እንጅሩ" ማለትን እንጂ ውሃ የሚሰጥ እምብዛም የለም ነበር።

በደረቀ ወንዛወንዝና የከብት እግር ባወጣው ጐርባጣ-ጎጥ መንገድም ጂፕና ላንድሮቨር የሚሄዱበት፣ ከዱከምና ከደብረዘይት አንስቶ እስከ ተራራው፣ ዝቋላ ጫፍ ድረስ የሚወስድ፣ የኣፈርና የኣሸዋ መንገድ አለ። ግን ያበደ ሾፌር ካልሆነ ማን ይሄድበታል! ስንሄድም፣ ስንመለስም መንገዱ ባዶውን ኣየን እንጂ ኣንዲትስ መኪና የሚባል ሲጓዝበት ፈጽሞ ኣላየንም።

ወደ ተራራው አካባቢ ስንጠጋም ጫካው ጥቅጥቅ እያለ፣ በታላላቅ ዛፎች፣ በዝግባና ደድሆ፣ ወይባና ቀጋ፣ ወይራና የኮሶም ዛፎች እየለበሰ መጣ። በተለይ ከኮሶ ዞፍ ላይ ያለው ብጫና ቀይ የሚያምር አበባና ፍሬው ከሩቁ ሆኖ በነፋሱ ወዲህና ወድያ ሲወዛወዝ ማየቱ እጅግ ደስ የሚል ነበር።

መንገዱን የጀመርነው በማለዳ ሲሆን ወደ ተራራው ዙርያ የተጠጋን ፀሓይ መራራ ሆና ወደ ተሲያት አካባቢ ነበር። ታድያ የሚያውቅ መሪ ካልያዙ ተራራውን መውጣት ቀላል አይደለም። ገደላ-ገደልና ጥቅጥቅ ያለ ዱርም ስለሆነ፣ አንዱን የከብት ወይም የጦጣ መንገድ ተከትሎ ቢኬድ፣ የጦጣ መንገድ ገደል ያደርሳል እንዲሉ፣ ከገደል አፋፍ ደርሶ ቀጥ ማለት ነው።

ደግነቱ አጋጣሚ ሆኖ አንድ መንገደኛ መነኩሴ አግኝተውን፣ እሳቸውም ከተራራው ጫፍ ወደሚገኝ የአቦ ገበረ-መንፈስ ቅዱስ ገዳም ተጓዥ ስለ ነበሩና፣ መንገዱንም ሄደውበት ኖረው በመጠኑ ስለሚያውቁት፣ እየመሩን ተራራውን ተያያዝነው። ያም ሆኖ ካንዴም ሁለቴ መንገዱን ለቅቀው በመሳታቸው ከገደል አፋፍ ደርሰን ለመመለስ መገደዳችንን አልረሳውም።

ከተራራው ጫፍ ስንደርስ ፀሓይ ወደመጥለቋ ገደማ ሆኖ፣ ለዓይን መያዝ ጀምሯል። ይሁንና የቤተክርስትያኑን አካባቢ ጐብኝተን ከተራራው ላይ ያለውንም ኩሬ ተመለከትን። ይህ ኩሬ መጠኑ ትልቅ ባይሆንም በዓለም በከፍተኛነት ቦታ ላይ ካሉት ኩሬዎች አንዱ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ምክንያቱም የአዲስ አበባ ከተማ ከባሕር በሰባት ሺሕ ጫማ ላይ ስትገኝ፣ ተራራውም በግምት ከዚያ ወደሦስትና አራት ሺሕ ጫማ ከፍ ስለሚል፣ ኩሬው በትንሹ ከዓስር ሺሕ ጫማ ከፍታ በላይ ይገኛል ማለት ነው።

በኩሬው ዙርያም ብዙ ታላላቅ ዛፎች ይገኛሉ፣ በዛፎቹም ብዙ ጦጣዎችና ጉሬዛዎች ከቅርንጫፍ ወደ ቅርንጫፍ እየዘለሉ ውር፣ ውር ይሉ ነበር። ከኩሬው በስተደቡብ/ምስራቅም አንድ ትልቅ የደንጊያና የአፈር ክምር አለ። የዚህም የዲንጋይ ክምር ድንቅ ምስጢር በማግሥቱ ነው የሰማነው።

ምሽቱን - ለካስ ዕለቱ የአቦ ገብረመንፈስ ቅዱስ ታቦት የሚከበርበት ዕለት ኖሯል፣ ቀን ከገዳሙ ትልቅ ድግስ ውሏል አሉን - መነኩሳቱና ካህናቱም “ምግብ ቀርቧል!” ብለው መኣድ አስቀመጡን፣ ማለፊያ የሆነ እራትም አቀረቡልን። እንጀራም፣ ወጥም፣ ጥሬ ስጋም፣ ጠላም፣ ምንም የቀረ የለም፣ በልተን፣ ጠጥተን ጠገብን። ከዚያም ለመኝታችን ተዘጋጀን…

በኢትዮጵያ ክፍለ-ሃገራት ስዞር የዚህ ዓይነቱ የነፃ ድግስ በብዙ ተደጋግሞ አጋጥሞኛል፣ ይህንም ሳስታውስ፤ “ለዚህ ለየዋሁ ወገኔ፣ ላበላኝ፣ ላጠጣኝ፣ ምን አደረግኹለት!” እያልኩ፣ ሁሌ የሚያሳስበኝ ጉዳይ ነው። ይቀጥላል…

ሰዎች በላይ ቦታ ባለመኖሩ፣ ሌሎቹ እያማረሩ ፊት ከነበሩበት ገላጣ ሜዳ መጥተው ተጋደሙ። ጎጆው ውስጥ ከገቡትም ሁለት ተማሪዎች ብዙ ሳይቆዩ "አረ ተባዩ ፈጀን!" እያሉ፣ በቁንጫና በቅማሉ እያማረሩ፣ ጥለው፣ ከሜዳው ይሻለናል በማለት ተመልሰው መጡ።

በብርዱ ቆፈን፣ በተባዩ፣ በኮረኮንች መሬቱ እየተሰቃየን፣ እንዳይነጋ የለም ነጋ። የማለዳ ፀሓይ እንደዚያን ሌሊት አምራን፣ በጉጉትም ናፍቀንናትና ተመኝተናት የጠበቅንበት ጊዜ ኣላስታውስም። ብልጭ እንዳለች ሁላችንም እየሮጥን ፀሓይ ወዳለችበት ጉብታ ኣምርተን ልንሞቅ ተቀመጥን። የማለዳ ፀሓይ ለካ እንዲህ ይጥማል! ጦጣውና ጉሬዛውም እንደኛው በየቅርንጫፉ ፀሐይ ሲሞቁ እናይ ነበርን። እነሱንም ለካ ብርድ ሲፈጃቸው ኣድሯል። በፀሓይ ሙቀት ነፍስ ዘርተን ለመንሰራራትና ለመንጠራራትም ቻልን።

ፀሓይ ስንሞቅ ከቤተክስያኑ የጥዋት ቅዳሴ ሲካሄድ ኖሮ፣ ረፈድ እንዳለ ተፈጽሞ፣ የዘኬ መክፈልት ሆነ። እኛም ከዚያው ሄደን የዳቦ ቁርስ በላን። ከቤተክስያኑ ጐንም ወደ ኣፋፉ ጠጋ ብለን ስናይ ከኣይሮፕላን ላይ ያለን ይመስል የኣድኣና የከረዩ ሜዳ ወለል ብሎ ተዘርግቷል። ከበስተሰሜን የኣዲስ ኣበባ ከተማ፣ ከጀርባውም የእንጦጦ ተራራ፣ ትንሽ ቀረብ ብሎም ወደ ምስራቅ በኩል የየረር ተራራ፣ ወደ ደቡብ ምስራቅም የደብረ-ዘይት ከተማና በኣካባቢዋ ያሉ ባሕሮች፤ ሖራ፣ ጨለቅለቃ፣ ብሽፍቱ፣ ኩሪፍቱ፣ ወዘተ... ትንንሽ ጉድጓዶች መስለው ይታያሉ። እጅግ ደስ የሚል ነበር።

ኣንድ ሽማግሌ መነኩሴም፤ "ለመሆኑ የዚህ ገዳምን ታሪክ ታውቃላችሁ?" ሲሉ ቀረቡን። ኣናውቅም ስንላቸው፤ "ድሮ የሰይጣን ምሽግ ነበር። ኣባ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ታድያ ቦታውን ሲያዩት ወደዱትና ወደ እግዚሃር ሄደው፤ 'ምነው ይህን ገነት የመሰለ ቦታ ለዲያብሎስ ሰጠኸው?' ኣሉት።

እግዚሃርም፤ 'እኔ መች ሰጠሁት፣ ራሱ ይዞት እንጂ!' ኣላቸው። ኣባ ገብረ መንፈስ ቅዱስም፣ 'በል ፍቀድልኝና ልቀማው?' ሲሉ ተማጠኑት። 'እሺ፣ ከቻልክማ ንጠቀውና ውሰዳ!' ኣላቸው። ኣባም ተነሱና ዲያብሎስን ጦርነት ገጠሙት። ይዘውም በመብረቅና በነጐድጓድ ሲሉት ጊዜ፣ ኣንድ እግሩን ቆረጡት። ሰይጣኑ ሲሸነፍ ታድያ፣ በእሳተ ነበልባል እየተፈጀ መሸሻውን ፈልጐ፣ በቀረችው እግሩ እንጣጥ ብሎ ዘሎ ባንድ እርምጃ ከሖራ ጥልቅ ብሎ ገባ። ትላንት ተዚያ ወድያ ያያችሁት የድንጋይ ክምርም የሰይጣኑ ቆራጣ እግር የተቀበረበት ነው።" ኣሉን። በጣም የሚደንቅ ጉድ ነው።

የሖራ ባሕር 'ቆሪጥ' የሚሉት ሰይጣን ኣለበት ተብሎ የሚወራውስ ለካ ለዚህ ኖሯል። ሁሉን ኣይተን፣ መነኩሳቱን ተሰናብተን፣ ወደ መጣንበት ልንሄድ ተነሳን። ከተራራው ለመውረድም ቁልቁለቱን ተያያዝነው።

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above story  are solely of the author and are not necessarily shared by** Meskot**. You may contact G.E.  Gorfu for comments at** gegorfu@yahoo.com**.***